# ንግድ ቻምበር የዜና መጽሄት

በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የመረጃና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ የዜና መጽሄት

ቁጥር 177

ከሰኔ 16—30 ቀን 2011 ዓ.ም.


## ዜና ቻምበር

## በውስጥ ገጾች


- **ፕሬዚደንቱ በካይሮ የፊሊፒንስ ... ገጽ 2**
- **የሌሎች ሸቀጥ ማራገፊያ ... ገጽ 2**


# ምክር ቤቱ ሁለት የማፀደቂያ ወርክሾፖችን አካሄደ






የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት **"የሀይል መቋረጥ በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪዎች እና የንግድ ድርጅቶች ላይ የሚያስከትለው ጉዳት እና 'የአፍሪካ አህጉር ነፃ የንግድ ቀጠና ለኢትዮጵያ የግል ዘርፍ የሚኖሩት እድሎችና ተግዳሮቶች"** በሚሉ ሁለት ርዕሶች ላይ በአዚማን ሆቴል የማፀደቂያ ወርክሾፖችን (Validation Workshops) አካሄደ፡፡

የማፀደቂያ ወርክሾፖቹ አላማ ተሳታፊዎች በጥናቶቹ በተለዩ ክፍተቶች እና በተቀመጡ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ላይ ሰፊና ጥልቅ ውይይት በማድረግ ጠቃሚ ሀሳቦችንና አስተያየቶች እንደያቀርቡና የጥናቶቹን ሰነዶች በማዳበር የጋራ አቋም እንዲዙ ለማድረግ እንደሆነ የገለፁት የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ፀሀፊ አቶ ውቤ መንግስቱ ሰነዶቹ በቀጣይ ከመንግስት ጋር ለሚደረገው የምክክር መድረክ ከሌሎች የግሉ ዘርፍ ዋና ዋና ችግሮች ጋር አብረው ለውይይት ይቀርባሉ ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ኢንጅነር መልአኩ እዘዘው የሀይል መቋረጥ በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪዎች እና የንግድ ድርጅቶች ላይ የሚያስከትለው ጉዳት በሚል ርዕስ ለተዘጋጀው የማፀደቂያ ወርክሾፕ መክፈቻ ስነ-ስርዓት ላይ እንደገለፁት የኤሌትሪክ ሀይል የሰውን ልጅ ኑሮ በማቅለል ለዘመናዊነትና ለአገር እድገት ጠቀሜታው ዘርፈ ብዙ ቢሆንም በሀገሪቱ የሀይል እጥረት መኖር ተጨማሪ በትራንስፎርመሮች መበላሸት፣ በኤሌትሪክ ምሰሶዎች መውደቅ፣ በሽቦዎች መበጣጠስ፣ በቴክኒክ ጉድለቶች እና በእውቀት ማነስ ምክንያት የሚከሰቱ የኤሌተሪክ ብልሽቶች የሚያስከትሉት የሀይል መቆራረጥ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ሞተር አንቀሳቃሽ የሆነውን የግሉን ዘርፉ የቢዝነስ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ እየጎዳው ይገኛል፡፡

ፕሬዚዳንት ጨምረው እንደተናገሩት ይህ የሀይል መቆራረጥ የማሽኖች መበላሸት፣ ምርትና አገልግሎት መቀነስ፣ ስራ ፈትነት፣ የጊዜ ብክነትን እና መሰል ችግሮችን በማስከተል የንግዱን ማህበረሰብ ለከፍተኛ ኪሳራ እያጋለጠ በመሆኑ ዘላቂ የሀይል አቅርቦት እንዲኖር ለችግሩ መፍትሄ በማበጀት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪ በዚሁ እለት ከሰዓት በኋላ ፕሮግራም ላይ ምክር ቤቱ የአፍሪካ አህጉር ነፃ የንግድ ቀጠና ለኢትዮጵያ የግል ዘርፍ የሚኖሩት እድሎችና ተግዳሮቶችን አስመልክቶ በተጠና የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ ላይም ውይይት አካሂዷል፡፡

ይህንን ውይይት አስመልክተው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ


ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# ፕሬዚደንቱ በካይሮ የፊሊፒንስ አምባሳደርን አነጋገሩ

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) ከምክትል ዋና ፀሀፊ አቶ ዉቤ መንግስቱ ጋር በመሆን በካይሮ የፊሊፒንስ አምባሳደር ሚስተር ሱልፒሽዮ ኮንፊላዶ ሰኔ 19 ቀን 2011 ዓ.ም. በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ፡፡

በካይሮ የፊሊፒንስ አምባሳደር ሱልፒሽዮ ኮንፊላዶ በኢትዮጵያና በፊሊፒንስ መካከል እዚህ ግባ የሚባል የንግድና የኢንቨስትመንት ግንኙነት እንደሌለ በመጥቀስ ለወደፊቱ በማኑፋክቸሪንግ፣ በመድሀኒት፣ በፍራፍሬና ጭማቂ፣ በፈርኒቸር፣ በቱሪዝም፣ በጨርቃጨርቅ እና መሰል ዘርፎች ላይ በሽርክና መስራት የሚፈልጉ የፊሊፒንስ ኩባንያዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ተናግረዋል፡፡ ከ20 በላይ አባላት ያሉት የፊሊፒንስ የቢዝነስ ልኡካን ቡድን ምክር ቤቱ በ2012 ዓም በሚያዘጋጀው የኢትዮ-ችምበር አለም አቀፍ የንግድ ትርኢት ላይ እንደሚሳተፉ በመግለፅ ሁለቱ አገሮች በቀጣይ የንግድና የኢንቨስትመንት ግንኙነታቸውን የሚያጠናክሩባቸው በርካታ እድሎች አሉ ብለዋል፡፡



የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጅነር) በበኩላቸው እንደገለጹት ኢትዮጵያ በርካታ የግብርና ምርቶች ስላሏት ለፊሊፒንስ ኤክስፖርት በማድረግ የፊሊፒንስንም ምርቶች ኢምፖርት በማድረግ ሁለቱ አገራት ለጋራ ጥቅም ግንኙነታቸውን በማጎልበት ረገድ ተባብረው መስራት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ሁለቱ አገሮች በሚያዘጋጁት የቢዝነስ ፎረሞች፣ ኤግዚቢሽኖች እና ንግድ ትርኢቶች ላይ የንግዱን ማህበረሰብ በማሳተፍ፣ መረጃ እንዲለዋወጡ፣ ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋወቁ በማድረግ የሁለትዮሽ ግንኙነታቸውን ማሳደግ ይችላሉ፡፡ ኢትዮጵያ ካሏት በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጮች በተጨማሪ አለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ በርካታ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እየተገነቡባት በመሆኗ የፊሊፒንስ ኩባንያዎች መጥተው ኢንቨስት ቢያደርጉ ውጤታማ እንደሚሆኑ ፕሬዚደንቱ ጨምረው ተናግረዋል፡፡

ሁለቱ አካላት በሁለቱ አገሮች መካከል ስለሚኖራቸዉ የንግድና ኢንቨስትመንት ትብብሮች እና በንግዱ ማህበረሰብ መካካል ስለሚኖረው የቢዝነስ ግንኙነት እንዲሁም ምክር ቤቱ በ2012 ዓም በሚያዘጋጀው የኢትዮ-ችምበር አለም አቀፍ የንግድ ትርኢት ላይ የፊሊፒንስ የቢዝነስ ልኡካን ቡድን በሚሳተፉበት አግባብ ዙሪያ ሰፊ ውይይት አካሄደዋል፡፡

# ‹‹የሌሎች ሸቀጥ ማራገፊያ እንዳንሆን የቤት ሥራችንን በአግባቡ ማከናወን አለብን›› አቶ መለኩ እዘዘው (ኢንጂነር)፣ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት

ከሪፖርተር፡ ሰኔ 16 ቀን 2011 ዓ.ም.፡- ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የማይተካ ሚና እንዳለው ይታመናል፡፡ በኢትዮጵያም የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሚና ይጎለብት ዘንድ ብዙ የተነገረ ቢሆንም፣ ውጤቱ ያን ያህል እንዳልሆነ በተደጋጋሚ ይገለጻል፡፡ በአሁኑ ወቅት የግል ዘርፉን ሚና ለማጎልበትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታን ለመፍጠር ይረዳሉ የተባሉ በርካታ ሕግጋት እየተሻሻሉ ነው፡፡ እነዚህ ማሻሻያዎች ከግል ዘርፉ አንፃር እንዴት እንደሚታዩ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት የግል ዘርፉን የተመለከቱ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ፣ ምን ዓይነት ፖሊሲዎችና ማሻሻያዎች እየተደረጉ ነው የሚሉ ጥያቄዎችም አሉ፡፡ እንዲሁም የንግዱ ማኅበረሰብ ጥያቄዎች እንዴት እየተመለሱ መሆናቸውንና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች በማንሳት፣ ዳዊት ታዬ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አቶ ፕሬዚዳንት መላኩ እዘዘው (ኢንጂነር) አነጋግሯል፡፡

**ሪፖርተር፡-** የንግድ ኅብረተሰቡን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከቱ ሕግጋት እየወጡና እየተሻሻሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የንግድ ምዝገባ አዋጅ፣ የጉምሩክ ቀረጥና የግብር አከፋፈል መመርያዎችና ሌሎች መሰል አዳዲስ ሕግጋቶችን እንዴት ይታያሉ? ከእነዚህ ሕግጋት መውጣት ጋር ተያይዞ የእናንተ ተሳትፎ ምን ነበር?

**ኢንጂነር መልአኩ፡-** አገራችን ኢትዮጵያ የቢዝነስ ሥራን ለማካሄድ እ.ኤ.አ. በ2018 በዓለም ባንክ በወጣው መረጃ ከ190 አገሮች መካከል 159ኛ የመሆናችን ሚስጥር የአሠራር ሥርዓቶቻችንና ሒደቶቻችን፣

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## ምክር ቤቱ ሁለት ....

ከገጽ 1 የዞረ





ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ኢንጅነር መልአኩ እዘዘው እንደተናገሩት የአፍሪካ አህጉር ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት ማርች 2018 ኪጋሌ ላይ ሲፈረም ከፈረሙት 44 አገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ እንደሆነች በማስታወስ ኢንዱስትሪያቸውን ያሳደጉ የአፍሪካ አገሮች ከስምምነቱ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ እና ያላሳደጉ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች ደግሞ ስምምነቱ የሚያስከትልባቸው ዕድሎችም ሆነ ፈተናዎች እንዳሉባቸው የሚናገሩ በርካታ ሙሁራን አሉ፡፡

ፕሬዚደንቱ አክለው እንደተናገሩት በውጪ አገር ምርቶች አገሪቱ እንዳትጥለቀለቅ ሀገራዊ ምርቶችን በማምረት ከሀገር አልፈው ወደ ውጪ ኤክስፖርት ማድረግ የሚችሉና ለአገር የውጪ ምንዛሬ የሚያመጡ አለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ኩባንያዎችን መፍጠር ይገባል፤ እንደ ንግዱ ማህበረሰብ ተወካይነቱ ይህ ሃላፊነት የምክር ቤቱ ስለሆነ ከስምምነቱ እንዴት ተጠቃሚ መሆን ይቻላል የሚለውን በአግባቡ ማየት ያስፈልገዋል፡፡

ሁለቱም ጥናቶች በየተራ ለተሳታፊዎች ከቀረቡ በኋላ ሀሳቦችና አስተያየቶች በግልጽ የተንሸራሸሩ ሲሆን ለተነሱ በርካታ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፤ ለጥናቶቹ ሰነዶች ማዳበሪያ የሚሆኑ ጠቃሚ ግብአቶችም ተሰብስበዋል፡፡

በወርክሾፖቹ ላይ የምክር ቤቱ የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት፣ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ሀላፊዎች፣ የግል ኩባንያዎች መሪዎች እና የባለድረሻ አካላት እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው በርካታ ተሳታፊዎች ተሳትፈዋል፡፡

## የሌሎች ሸቀጥ ማራገፊያ .......

ከገጽ 2 የዞረ

ሕጎቻችንና መመርያዎቻችን ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ አገር ባለሀብቶች ምቹ የኢንቨስትመንትና የንግድ መዳረሻ አገራችንን ከማድረግ አንፃር፣ ምክንያታዊነታቸው ተቀባይነት የሌለውና አሉታዊ አስተሳሰብን ብቻ መሠረት እያደረጉ የሚወጡ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመርያዎችን ማሻሻልን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ አንፃር በገቢዎች ሚኒስቴር፣ በብሔራዊ ባንክ፣ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አማካይነት እየወጡ ያሉ መመርያዎችና የአዋጅ ማሻሻያዎች መጪውን የቢዝነስ ምኅዳር ጊዜ ተስፋ ሰጪ እያደረጉ ናቸው፡፡ የንግዱ ማኅበረሰብ ተስፋ ቆርጦ አይቀየሩም ያላቸው ጉዳዮች በማሻሻያ እየተካተቱ በማየታችን ጅምሩን እያደነቅን፣ በቀጣይ ሰፋ ያሉ አገራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሊያመጡ የሚችሉ አሠራሮች እንደሚተገበሩ ተስፋ አለኝ፡፡ በገንዘብ ሚኒስቴርና በገቢዎች ሚኒስቴር በኩል የወጡት ከሃያ ያላነሱ መመርያዎች ከመፅደቃቸው በፊት ረቂቆቻቸው በምክር ቤታችን ተልከው ለእኛ ባለሙያዎችና አባላትም በማካፈል አስፈላጊውን ግብዓት ሰጥተናል፡፡ በንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤታችን የምርምርና አድቮኬሲ ዳይሬክቶሬት አማካይነት ሁሉም ባይደርሱንም፣ የንግዱ ማኅበረሰብ ድምፅ እንደ መሆናችን አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡ በተለይ የንግድ ሥራን ለማካሄድ የሚያስችል ለማድረግ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት ሁሉም የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የድርሻቸውን እየወሰዱ የአዋጆችን የደንቦችንና የመመርያዎችን ጠንካራ ደካማ ጎን በመፈተሽ፣ የማሻሻያ ሐሳቦችን በማክል ደረጃችንን ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት በእጅጉ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡

**ሪፖርተር፡-** የንግድ ኅብረተሰቡ ሊሻሻልልኝ ይገባል ብሎ ከዚህ ቀደም ያቀርባቸው የነበሩ በርካታ ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ እናንተም በጥናት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎችን ጭምር በንግድ ምክር ቤቶቻችሁ በኩል ስታቀርቡ እንደ መቆየታችሁ መጠን፣ እስካሁን ምን ምላሽ አግኝታችኋል? በተለይ ከለውጡ ወዲህ የንግድ ኅብረተሰቡ አንገብጋቢ ጥያቄዎችን ይዛችሁ መልስ እንዲያገኙ ያደረጋችሁት ጥረት አለ? ምን ተገኘ?

**ኢንጂነር መልአኩ፡-** የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በየሁለት ዓመቱ አገራዊ የቢዝነስ አጀንዳ ጥናት ያከናውናል፡፡ ያለፈው ዓመት ጥናት ውጤትም በአገሪቱ ያለውን የንግድና ኢንቨስትመንት ምኅዳር ተግዳሮቶች በቅደም ተከተል ያስቀምጣል፡፡ ይህ ውጤት የዓለም ባንክ የአገራችን የንግድ ሥራ ያለውን ቅለት ከሚለካበት መሥፈርት ጋር ተቀራራቢ ውጤቶችን ያሳያል፡፡ የአገራዊ ቢዝነስ አጀንዳ ጥናታችን ውጤት 13 ያህል ተግዳሮቶችን በቅደም ተከተል አስቀምጧል፡፡ እነዚህም የንግድ ሥራ በመጀመር ያሉ ችግሮች የመሠረተ ልማት (ኤሌክትሪክ፣ ውኃ) አገልግሎት፣ የመሬት አቅርቦትና የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፣ መልካም አስተዳደር፣ የብድር ፖሊሲ አቅርቦትና ተደራሽነት፣ የታክስ ፖሊሲና አስተዳደር፣ ተዓማኒ የገበያ መረጃ አለመኖር፣ የንግድ ፖሊሲ፣ የትራንስፖርት ፖሊሲና አቅርቦት፣ የኮንትራት ስምምነቶች አስገዳጅነት፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል አለመኖርና የመጨረሻው የፖለቲካ አለመረጋጋት ናቸው፡፡

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

**የሌሎች ሸቀጥ ማራገፊያ .......** **ከገጽ 3 የዞረ**



ከእነዚህ 13 የንግዱ ማኅበረሰብ ተግዳሮቶች መካከል ሰሞኑን የፀደቀው 1150/2011 የንግድ ፈቃድና ምዝገባ አዋጅ የንግድ ሥራን ለመጀመርም፣ ለማከናወንም፣ ለመዝጋትም ያለውን ችግር ሊፈታ በሚችል መንገድ መውጣቱ ጥሩ ነው፡፡ የንግዱ ማኅበረሰብ ከገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ባለሙያዎችና ኦዲተሮች ጋር ሁልጊዜ የሚያጨቃጭቃቸው ከሒሳብ መዝገብ አያያዝና ከግብር፣ እንዲሁም ጉምሩክ ክፍያ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተብራራና ግልጽ ሊያግባቡ በሚችሉ መንገዶች መመርያዎች መቃኘታቸው ለገቢዎች ሚኒስቴርና ለገንዘብ ሚኒስቴር ጅምሩ ጥሩ ነው፡፡ የቀሩትንም በዚህ ፍጥነት መሥራት ከቻልን ከንግዱ ማኅበረሰብ ዕርካታ በተጨማሪ፣ የዓለም ባንክ የንግድ ሥራ ጅማሮ ቅለት ደረጃን በማሻሻል አገራችንን የንግድና ኢንቨስትመንት መደረሻ ማድረግ እንችላለን፡፡ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ በመሪነት እንቀጥላለን፡፡ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከአገራዊ ቢዝነስ አጀንዳ ጥናት በተጨማሪ፣ ከክልል ክልል የቢዝነስ አጀንዳዎችና ተግዳሮቶች ባላቸው የተፈጥሮ ሀብት፣ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ፣ የቆዳ ስፋትና ሌሎችም መሥፈርቶች ሊለያዩ ስለሚችሉ የአምስት ክልሎችን ክልላዊ ቢዝነስ አጀንዳ ማለትም ትግራይ፣ የአማራ፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ፣ የኦሮሚያና የሐረሪ ክልሎችን አስጠንተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአገራዊ ቢዝነስ አጀንዳ የተለዩትን ሁለቱን ችግሮች፣ ማለትም የመሬት አቅርቦትና የኤሌክትሪክ መቋረጥ በንግዱ ማኅበረሰብ ፈጠረውን ችግር በአገር ደረጃ ያለውን ተፅዕኖ በስፋትና በዝርዝር አስጠንተናል፡፡ በሌላም በኩል የደን ሀብት፣ የቢዝነስ ዕድሎችና ተግዳሮቶች በተመለከተ በአራቱም ክልሎች ጥናት አሠርተናል፡፡ እነዚህ ሁሉ የጥናት ውጤቶች በቅርቡ በሚኖረን የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የምክክር መድረክ ለውይይት በማቅረብ ከመንግሥት ጋር ውይይት እናደርግባቸዋለን፡፡

***ሪፖርተር፡-*** ትልልቅ የሚባሉ ኩባንያዎችን ሙሉ በሙሉና በከፊል ወደ ግል ለማዛወር የሚያስችሉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የንግድ ምክር ቤታችሁ ሚና ምን ድረስ ነው ማለት ይቻላል? እነዚህን ኩባንያዎች የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ሊገዙ የሚችሉበት ዕድል ምን ያህል ነው ብለው ያምናሉ? መንግሥት በብርቱ ሊያስብበት ይገባል ብለው የሚያምኑበት ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ በምን መልኩ መቃኘት አለበት?

**ኢንጂነር መልአኩ፡፡-** ከዚህ በፊት በፍፁም በድርድር አይቀርቡም ይባሉ የነበሩ ተቋማትን ወደ ግል ለማዛወር መንግሥት መወሰኑ በሀብት ማሰባሰብ፣ በአገልግሎት ጥራት፣ በዕውቀት ሽግግር፣ በልምድ ልውውጥና በፍትሐዊ የገበያ ውድድር የሚኖረው ሚና ትልቅ ቢሆንም፣ በሒደት የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በማየት ሁሉንም በአንድ ጊዜ ባለመፈጸም ትምህርት በመውሰድ ሊከወን የሚገባው ስስ ጉዳይ ነው፡፡ በአገልግሎት አሰጣጣቸውና በጥራት ተወዳዳሪነታቸው የሚዶድላቸው ተቋማት ወደ ግል የመዛወራቸው ዓላማ ደንበኛው ያልተቆራረጠና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኝ ከማስቻሉም በላይ፣ ደንበኛው አማራጭ አገልግሎት በተወዳዳሪ ዋጋ ማግኘቱና በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ምንዛሪ የካፒታል ዕድገት መፍጠር ነው፡፡ ለምሳሌ ኢትዮ ቴሌኮም ብቸኛ ተቋም በመሆኑ አገልግሎቱን እያገኘን ቢሆንም፣ አገልግሎት አሰጣጡን በየጊዜው በማሻሻል የዋጋ ታሪፍ ቅናሽ እያከናወነ አንድ ለእናቱ ተቋም በመሆኑ በአገልግሎቱ በአግባቡ አልረባንም፡፡ በተለይ በዚህ ዘመን ሁሉም የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን ከስልክና ከኢንተርኔት ጋር በመያያዙ የሰዓታት መቆራረጥና የአገልግሎት አሰጣጥ መስተጓጎል፣ ራሱን በየጊዜው የማያዘምን ቴክኖሎጂ ዓለም ወደ አንድ መንደር እየተቀየረች በመጣችበት በዚህ ዘመን ተወዳዳሪ አያደርገንም፡፡

በመሆኑም አሁን መንግሥት በያዘው አቅጣጫ የአንበሳውን ድርሻ በመያዝ የተወሰነውን እየለቀቀ፣ ውጤቱን እየገመገሙ፣ ተሞክሮውን ለሌሎች ተቋማት እንዴት ሊያስተላልፍ እንደሚችል በመሰነድ ሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶችም መጥተው ሊሠሩ የሚችሉበት የሕግ ማዕቀፍ በማፅደቅ የተጀመረው ሥራ መልካም ነው፡፡ እንዲሁም ዘው ብሎ በመግባት አተርፍ ባይ አጉዳይ እንዳይሆን፣ አሥር ጊዜ በመለካት አንድ ጊዜ መቁረጥ የሚለውን የአበውን

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## የሌሎች ሸቀጥ ማራገፊያ .......

ከገጽ 4 የዞረ

ብሂል መጠቀም ጥሩ ነው:: ተቋማትን ወደ ግል ለማዛወር በሚደረግ ሒደት መንግሥት አማካሪ ቦርድ ማቋቋሙ ያልታዩና ያልተገመቱ ዕይታዎች ጎልተው እንዲወጡ ከማድረግ ባሻገር፣ የምሁራንና የሕዝቡን አስተያየት መንግሥት የሚቀበልበት መንገድም ነው::

**ሪፖርተር**፡- እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ያሉት በዚህ ሒደት መጓዝ የለባቸውም የሚል አስተያየት ይሰጣል:: የእርስዎ ምልከታስ? የመንግሥት ተቋማት ወደ ግል ሲዞሩ ኢትዮጵያውያን የንግድ ሰዎች በዚህ ዕድል እንዲጠቀሙ ምን ታስቧል?

**ኢንጂነር መልአኩ**፡፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከብሔራዊ ምልክትነቱ በተጨማሪ በአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት፣ በትርፋማነት፣ በዓለም አቀፍ ብራንድና በብዙ መሥፈርቶች የምንኮራበት ተቋም እንደ መሆኑና በአሁኑ ጊዜ ተቋሙ ከሌሎች አየር መንገዶች ጋር አክሲዮን በመግዛትና በሽርክና እየሠራ ባለበት ሁኔታ ወደ ግል የማዛወሩ ሒደት ቆም ብለን ማጤን እንዳለብን ያመላክተናል:: የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በዚህ ተግባር ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉባቸውን መስኮች፣ በተለይ እኛ እንደ የንግድ ማኅበረሰብ ተወካይነታችን በማስተባበርና ግንዛቤ በመፍጠር የንግዱ ማኅበረሰብ በዚህ ሒደት ላይ እንዲሳተፍ ለመሥራት አስበናል:: ለምሳሌ በቅርብ የተቋቋመው ኢትዮ ስኳር ማኑፋክቸሪንግ አክሲዮን ማኅበር የስኳር ፋብሪካዎችን ለመግዛት የተቋቋመ ነው:: ከውጭ አገር ድርጅት ጋር በጋራ በመሆን ራሱን እያዘጋጀ ያለው በቻምበር አባላት አስተባባሪነት ነው:: እነዚህን ተቋማት ወደ ግል በማዛወር ከሚደረገው ሒደት በፊት፣ መንግሥት የአክሲዮን ገበያን አሠራርና ዓለም አቀፍ የፋይናንስ አመዘጋገብ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ ያለበት ይመስለኛል:: በአገራችን በብዙ ግለሰቦች እጅ ገንዘብ አለ:: ይህንን በሕግ ማዕቀፍ የሚያሰባስብና የሚያቀናጅ ሲስተም ተፈጥሮ ኩባንያዎችን መፍጠር የሚችል አቅም ነው:: እንዲሁም በግሉ ዘርፍ ከፍተኛ የካፒታል አቅም መሆን ይቻላል:: ከባንኮችና ከኢንሹራንሶች አክሲዮን ውጪ በሌሎች አክሲዮኖች ላይ ተሳታፊ በመሆን ብዙም የማይተጋው የአገራችን ሕዝብ ለዚህ ነው:: መንግሥት የስቶክ ማርኬት ሲስተም በአገራችን እንዲፈጠር በማድረግ በየባንኩ በግሸበት እየተመታ የሚገኘውን ገንዘብ፣ እንዲሁም በጊዜ ገደብ እየተቀመጠ ወለድ ብቻ የሚሰበሰበውን ገንዘብ ወደ ኢንቨስትመንት በመቀየር ለሥራ ዕድል ፈጠራና ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ ይቻላል:: ሁሉም በየአቅሙ ባለው ገንዘብ ልክ የኩባንያ ባለቤት እንዲሆንና በሕግ ተጠያቂነት መሠረት የሚሠሩ ኮርፖሬሽኖች መፍጠር የስቶክ ማርኬት ዓላማ ነው:: ስለዚህ ግዙፍ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ለማዛወር ሲታሰብ፣ ይህ የስቶክ ማርኬት ሲስተም ቢቀድም መንገዱን ያቀለዋል:: ሌላው ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ አመዘጋገብ ሥርዓት ጋር በተያያዘ፣ ድርጅቶች ግልጽነትና ተጠያቂነት በተሞላበትና ዓለም አቀፍ ስንታንዳርድ ባለው መንገድ የሒሳብ መዝገብ አያያዛቸው መቃኘት አለበት::

**ሪፖርተር**፡- እንዴት?

**ኢንጂነር መልአኩ**፡፡- ለዚህም በአገራችን የኢትዮጵያ አካውንቲንግ ኦዲት ቦርድ የሚባል ተቋም በሕግ ተቋቁሞ፣ ደረጃ በደረጃ ተቋማት ይህንን እንዲተገብሩት ማድረግ ጀምረዋል:: እስካሁን የፋይናንስ ተቋማት የሆኑት ባንኮችና ኢንሹራንሶች ወደዚህ ሲስተም የገቡ ሲሆን፣ ዘንድሮ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ራሳቸውን እያዘጋጁ ነው:: እንዲሁም ዓመታዊ ገቢያቸው ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ የግል ድርጅቶችም በሚፈጥሩት የሥራ ዕድል በሚከፍሉት ግብርና በኢኮኖሚው ባላቸው አስተዋጽኦ፣ እዚህ ሲስተም ውስጥ እንዲገቡ ድረስ አሥር ዓመት ያዛል:: ይህ መሆኑ የድርጅቶች የፋይናንስ አቋም ምን እንደሆነ በግልጽ ቢታወቅ፣ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ባለሀብቶች አክሲዮን ለመግዛት ለውሳኔ ይረዳቸዋል:: የውጭ አገር ኢንቨስተሮች በሽርክና በጋራ ለመሥራት በሚያቀርቡት ጥያቄም፣ የአገራቸውን አጠቃላይ ኩባንያ ፕሮፋይል ተረድተው መወሰን የሚችሉት በዚህ መንገድ ሲቃኝ ነው:: ያለበለዚያ ባህላዊና ልማዳዊ አሠራር እንደ ውቅያኖስ የሰፋውን ሰፊ ዓለም አቀፍ የተወዳዳሪነት ምኅዳር ተሻግረን ከፈለግንበት ግብ ሊያደርሰን አይችልም:: እንደ ቻምበር ይህንን ጉዳይ አሁን እያዘጋጀን ባለው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ፕላን፣ (2012 – 2018) እነዚህንና መሰል ጉዳዮችን የንግዱ ማኅበረሰብ ግንዛቤ እንዲኖረው በማድረግ፣ ጠንከረን የምንሠራበትንና የፊት ተዋናይ የምንሆንበትን መንገድ ቀይሰን እንንቀሳቀሳለን::

**ሪፖርተር**፡- ኢትዮጵያ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና እንዲመሠረት ይሁንታ ሰጥታለች:: የዚህ ነፃ የንግድ ቀጣና መፈጠር አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች እንዳሉት ይገለጻል:: እንደ ንግድ ምክር ቤት መሪነትዎ የእርስዎ ምልከታ ምንድነው?

**ኢንጂነር መልአኩ**፡፡- በአገሮች መካከል የሚከናወን የንግድ ግንኙነትና ድርድር አገሮች ቋሚ ዕድገትን ለማስመዝገብ፣ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ፣ እንዲሁም የአገራቸውን ሕዝብ ከድህነት ለማውጣት፣ የተሻለ ዋጋ ለማግኘት፣ በገቢና በወጪ ንግዱ መካከል ያለውን የንግድ ሚዛን ለመቀነስ አስተዋጽኦው የጎላ ነው:: በዓለም አቀፍ የንግድ ሥርዓት ተጠቃሚ ያደርጋል፣ ልማትንም ያረጋግጣል:: ባለፉት 25 ዓመታት አገራችን ኢትዮጵያ የንግድ ግንኙነቷን ለማጠናከር ከሃያ አገሮች ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት ተፈራርማለች:: ከአፍሪካ አኅጉር 12፣ ከእስያ አምስት፣ ከአውሮፓ ሁለትና ከደቡብ አሜሪካ አንድ በዓለም ላይ ወደ 400 የሚደርሱ አካባቢያዊ ውህደቶች ሲኖሩ፣ በአፍሪካ ደግሞ ወደ ስምንት የሚደርሱ በአፍሪካ ኅብረት ዕውቅና የተሰጣቸው አካባቢያዊ ውህደቶች አሉ::

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## የሌሎች ሸቀጥ ማራገፊያ ....... ከገጽ 5 የዞረ

የአፍሪካ አኅጉር ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት በአገሮች ብዛት በሚሸፍነው 1.2 ቢሊዮን ሕዝብ ከዓለም ትልቁ ውህደት ያደርገዋል፡፡

**ሪፖርተር፡**- በነፃ ንግድ ቀጣናው መፈጠር የኢትዮጵያ የግል ዘርፍ ተጎጂ ይሆናል ተብሎ ከሚሠጋበት አንዱ መንግሥት ለግል ዘርፉ ይሰጥ የነበረውን ድጋፍና ከለላ ያሳጣዋል የሚል ነው፡፡ ይህ እንዴት ይታያል?

**ኢንጂነር መልአኩ፡፡**- እስካሁን ባለን መረጃ የእኛ መንግሥት ከፍተኛ ተደራዳሪዎች የአገሪቱን ጥቅም በሚያስጠብቅ ደረጃ የንግዱን ማኅበረሰብ አቅምና ተወዳዳሪነት፣ እንዲሁም የአገራችንን የዕድገት ደረጃ መሠረት በማድረግ ድርድሩ በማከናወን ላይ ናቸው፡፡ ይህ ውህደት ከተጠቀምንበት ዕድል ካልተጠቀምንበት ደግሞ ተግዳሮት ነው፡፡ ልክ እንደ እሳት አድርገህ ውሰደው፡፡ እሳት በመጠኑ በማድረግ ከተጠቀምክበት ምግብ ያበስላል፣ የበረደውን ያሞቃል፣ ሌላም፣ ሌላም፡፡ በአግባቡ ካልተጠቀምክበት ደግሞ ደን ያቃጥላል፣ ንብረት ያወድማል. . . ስለዚህ ይህ ዕድል ይዞት የሚመጣው በርካታ ነገር አለ፡፡

**ሪፖርተር፡**- ምን ዓይነት ዕድሎች? ተፅዕኖውስ?

**ኢንጂነር መልአኩ፡፡**- ለምሳሌ ለአገራችን ምርቶች ሰፊ የገበያ ዕድል ይፈጥራል፡፡ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ግብዓቶችንና ውጤቶችን ማግኘት የሚቻልበት መንገድ ይኖራል፡፡ አሁን ካለው የበለጠ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ሊጨምር የሚችልበት አጋጣሚም ሰፊ ነው፡፡ እንዲሁም በዛ ያለ የሥራ ዕድል ሊፈጠር ይችላል ብለን እናምናለን፡፡ ተግዳሮቶችን ስንመለከት የታሪፍ መቀነስን ተከትሎ የመንግሥት ገቢ ሊቀንስ ይችላል፡፡ የኢንዱስትሪዎቻችን ተወዳዳሪነት ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ ምንም እንኳን የታሪፍ መቀነስ ቢኖርም በአገሮች መካከል በሚኖረው የንግድ እንቅስቃሴ ምክንያት፣ አገሮች ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ገቢያቸው በአራት እጥፍ ሊያድግ እንደሚችል ጥናቶችና ትንበያዎች ይናገራሉ፡፡ «ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም» እንደሚባለው አሁን ፈርመናል፣ ገብተናል፡፡ በዚህ ሰፊ ውቅያኖስ ውስጥ እንደ መግባታችን የዘርፉን ተዋናዮች ኅበዝ ዋናተኛ አድርጎ መቅረፅ ይገባል፡፡ በተዋናዮች መሠራት ያለበት ጉዳይ ምንድነው? የሚለውን በአግባቡ ማጤን አለብን፡፡ ልክ እንደ እሳቱ የአፍሪካ አኅጉር ነፃ የንግድ ቀጣናን ዕድሎቹን አሟጠን ልንጠቀም የምንችለውና ተግዳሮቶቹን መሻገር የምንችለው ምን ተግባራት ብናከናውን ነው? እንደኛ የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ ችግሮች መፍታት መቻል አለብን፡፡ በገንዘብ አቅርቦት፣ በኤሌክትሪክ ኃይል፣ በምርት አመራረት ጥራት፣ በትራንስፖርትና በሎጂስቲክስ፣ በጥሬ ዕቃ አቅርቦትና በመሳሰሉት ያሉበት ችግሮች ተፈትተው ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ አምራች መፈጠር አለበት፡፡ ያለፉትን ዓመታት የአገራችን የንግድ ልውውጥ ከአፍሪካ አገሮች ጋር ስንመለከተው ከአሥር በመቶ የማይበልጥ፣ እንዲሁም ጥሬ የግብርና ምርቶች መላክ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆን ብቻ ሳይሆን፣ አጠቃላይ ኤክስፖርት ከዓመት ወደ ዓመት እቀነሰ የሚሄድ መሆኑና የውጭ አገር ምርቶች በአገራችን ገበያ በብዛት ማየታችን በተወዳዳሪነታችን ላይ ጥያቄ ያስነሳል፡፡

**ሪፖርተር፡**- ታዲያ እነዚህን ችግሮች ለመቀነስ ወይም ለመፍታት ምን መደረግ አለበት?

**ኢንጂነር መልአኩ፡፡**- እነዚህን ችግሮችን በመፍታት ካልሠራን የአፍሪካውያን ብቻ ሳይሆን፣ የሌሎችም የሸቀጥ ማራገፊያ እንዳንሆን ከአሁኑ የቤት ሥራችንን መሥራት አለብን፡፡ በተለይ ጥሬ የግብርና ምርቶች ብቻ መላክ መሠረት ያደረገው ኤክስፖርት እሴት ተጨምሮ እንዲላክ በማድረግ፣ መግዛት የሌለብንንና የምናስመጣቸውን ዕቃዎች ማሰብ፣ የውጭ አገር ምርቶችን ሊተኩ በሚችሉ ምርቶች ላይ ማተኮርን ይጠይቃል፡፡ ገበያውን ከማጥናት አኳያ ከየትኞቹ የአፍሪካ አገሮች ጋር ነው የጋራ የንግድ ልውውጥ ልናደርግ የምንችለው? የትኞቹ አገሮች ምን ይፈልጋሉ? ከየት ነው የሚያስመጡት? በትራንስፖርትና በሎጂስቲክስ ወጪ የሚቀነስልንና ተወዳዳሪ ሊያደርገን የሚችል ምን ዓይነት ምርት ለየትኛው አገር ነው የሚለውን በአግባቡ ማጥናት ይጠይቃል፡፡ አገራችን ተወዳዳሪ ሊያደርጓት የሚችሉ ምርቶች በአጭር፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜ ምንድናቸው? የእኛ አገር አንፃራዊ ዕድል ምንድነው? በየትኛው እናተኩር? ብዙ ድስት ጥዶ ሁሉንም ከማሳረር፣ የተወሰኑት ላይ በማተኮር ውጤታማ መሆን ይቻላል፡፡ ይህ ስምምነት ሰፊ የገበያ ዕድል እንደ መፍጠሩ፣ እኛም ምርቶቻችንን በብዛት በማምረት ከጥራት ጋር ማቅረብ ካልተቻለ ደንበኞች ወደ ሌላ አገር ዓይናቸው ሊዞር ስለሚችል በብዛት ማምረት ላይ ማተኮር ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም በተለያዩ ሴክተሮች ያለንን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት የትኞቹን ለመከላከል፣ የትኞቹን ለውድድር ለማቅረብ ዝርዝር ስትራቴጂ ማዘጋጀት አለብን፡፡

**ሪፖርተር፡**- ለምሳሌ በየትኛው ዘርፍ?

ኢንጂነር መላኩ፡- ለምሳሌ አገራችን በቆዳና በቴክስታይል ዘርፎች ተወዳዳሪ መሆን እንደምትችል ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በተመሳሳይ ሌሎች መስኮች ፋርማሲዩቲካል፣ የተቀነባበሩ የግብርና ምርቶችና ሌሎችንም በየዘርፋቸው በዝርዝር በማጥናትና አቋም በመያዝ በስትራቴጂው ማካተት አለብን፡፡ የአገር ውስጥ ባለሀብት ሁልጊዜ በአጥር ተሸብቦ በመከላከል ብቻ መቀጠል እንደማይቻል በማስገንዘብ በእኛ በቻምበርም፣ በመንግሥትም በመሥራት ራሳቸውን ወደ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ደረጃ በማሳደግ የበቁ፣ የነቁ፣ የተደራጁ፣ የተወዳዳሪነት መንፈስ ያላቸው፣ ውድድርን በአሸናፊነት ለመወጣት ውስጣዊና ተቋማዊ ዝግጅት ያላቸው፣ የዓለምን የገበያ መረጃ በመዳፋቸው በየቅጽበቱ የሚከታተሉ፣ አገራዊ ስሜት ያላቸው፣ የአገራቸውን

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## የሌሎች ሽቀጥ ማራገፊያ ....... ከገጽ 6 የዞረ

ጥቅም የሚያስቀድሙ ዓለም አቀፍ ብቃት ያላቸው ነጋዴዎች ሲፈጠሩ ይገባል። ልጅ እንደተወለደ ራሱን ችሎ መራመድ፣ መብላትና መጠጣት እስከሚችልበት ጊዜ ድረስ የእናት እንክብካቤ እንደማይለየው፣ መንግሥት የግሉን ዘርፍ ራሱን ችሎ መወዳደር እስከሚችልበትና አቅም እስኪገነባ ድረስ እንደ እናት የመንከባከብ፣ በሕጎችና ደንቦች በመደገፍ የማብቃትና የማገዝ ሚና ቢኖርበትም ለዕድሜ ልክ ከዓለም አቀፉ የገበያ ንግድ ተወዳዳሪነት ከልሎ ሊያስቀምጠው አይችልም። ይህ ለንግዱ ማኅበረሰብ እየተደረገ ያለው ጥበቃና ከለላ አቅም እስከንገነባ፣ ራሳችንን እስከንችል፣ ተወዳዳሪ የመሆን አቅማችን ከፍ እስኪል ድረስ መሆኑ ባያጠያይቅም፣ መንግሥትም ነጋዴውን ሳያስታጥቅ ዝም ብሎ የንግድ ውድድር ውስጥ ግባ አይለውም።

ለተወዳዳሪነት በመንግሥት በኩል በመተግበር ያሉ አዳዲስ የአዋጅ ማሻሻያዎችን ጨምሮ፣ ከኤክስፖርት ጋር በተያያዘ ባለድርሻ አካላት ለሆኑ ተቋማት በአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እየተተገበረ ያለው ፕሮጀክት ለሥምሪቶቻችንና ለተወዳዳሪነት አስተዋጽኦ አለው። በቀጣይነት በመንግሥት በኩል የሚከናወኑ ከድርድር ጋር በተያያዘ በርካታ ተግባራት አሉ። ከእነዚህም መካከል በታሪፍ ሊብራላይዜሽን ላይ የሚደረግ ድርድር፣ የዕቃዎች ሥሪት ምንጭ (Rule of Origin) ድርድር ላይ መሳተፍ፣ ማለትም አንድ ምርት የዚያ አገር ነው የሚባለው ምን ያህል ፐርሰንት የአገሩን ጥሬ ዕቃ ሲጠቀም ነው? ለምሳሌ ሁሉንም ጥሬ ዕቃ ከውጭ አገር አስገብቶ የሚጨምረው እሴት አሥር በመቶ ብቻ ቢሆን የዚያ አገር ምርት ይባላል ወይ? እና የመሳሰሉት ውይይት ይካሄድባቸዋል። የአኅጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ሴክረታሪያት ይቋቋማል። የአፍሪካ የግሉ ማኅበረሰብ ያለበት ቢዝነስ ካውንስልም ይቋቋማል። እኛም ተሳትፎ እናደርጋለን። በቅርቡ ኒጀር በሚካሄደው የመሪዎች ጉባዔም የአፍሪካ ቢዝነስ ዱባይ ስድስት ስብሰባዎች ይኖሩናል። የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ንግድ አቅርቦት ማዘጋጀት የድርድር አካል ነው። እንደ ቻምበር ከመንግሥት ጋር በመሆን ለንግዱ ማኅበረሰብ ይህ ስምምነት ያለውን ጠቀሜታ በማስረዳት ዝግጁ እንዲሆኑ፣ በመጪዎቹ ጊዜያት ጠንክረን የምንሠራበት ጉዳይ ነው። በተለይ አዎንታዊ ተፅዕኖዎቹን በማጉላት ከስምምነቱ ተጠቃሚ የምንሆንበትን መንገድ በመቀየስ የንግዱን ማኅበረሰብ ማዘጋጀት ትልቁ የቤት ሥራችን ነው። በመጪው ዓመት ስትራቴጂ በመንደፍ አገራዊ የግንዛቤ ፈጠራና ዝግጅት ሥራ በማከናወን፣ በአገር ውስጥ በአገልግሎትና በንግድ ላይ ብቻ መሠረት አድርጎ መንቀሳቀስ የሚወደውን የንግድ ማኅበረሰብ ተወዳዳሪ መሆን የሚቻለው፣ ኢንዱስትሪው በአገር ውስጥ ሲጎለብት መሆኑን ማስረዳትና ጥሬ የግብርና ምርት መላክ ውጤታማ እንደማያደርግ፣ አስመጪነትን መሠረት በማድረግ የሚከናወን የወጪ ንግድ (Export) መጪውን አኅጉራዊ ውድድር በድል አድራጊነት ለመወጣት ብቃትና ወሳኝነት እንዳለው ማስረዳት፣ ማስገንዘብና ማስረፅ የእኛ ሥራ ነው።

***ሪፖርተር፡-*** የአገሪቱ ኢኮኖሚ ፖሊሲ እንዴት ቢቃኝና ምን ቢደረግ የተሻለ ይሆናል ብለው ያምናሉ?

**ኢንጂነር መልአኩ፡-** መንግሥት አገራችን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር በኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ፣ በፌዴራልና በክልል ደረጃ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች፣ በግዙፍ የስኳር ፕሮጀክቶች ልማት ላይ አተኩሮ እየሠራ መሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም የአገራችን አንፃራዊ ዕድሎች (Comparative Advantages) የሚባሉትን የበለጠ ትኩረት በመስጠት ኢንዱስትሪውን ማጉላት ይቻላል ብዬ አምናለሁ። በግብርናና በእንስሳት ሀብት ልማት ላይ መሠራት አለበት። እንዲሁም በደን ሀብት ልማት ላይ መሠራት ይኖርበታል። ግብርናውን ስንመለከት ለሺሕ ዓመታት በበሬ እየተሳበ ለዕለት ፍጆታ የሚውል በማምረት የትም አላደረስም። ከ60 ሚሊዮን ሔክታር ያላነሰ መታረስ የሚችል መሬት ይዘን 20 በመቶ ብቻ እያረስን መሬት ፆም እያደረ ነው። ቀድሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ 30 ሚሊዮንና 40 ሚሊዮን እያለ ይመግበው በነበረ ገበሬ፣ ዛሬ 100 ሚሊዮን ያለፈውን ሕዝብ ለመመገብ ያለ ግብርና ሜካናይዜሽን የሚታሰብ አይደለም። 85 በመቶ ሕዝብ በግብርና የሚተዳደር ነው እያልን፣ አገራችን የውኃ ማማ ናት እያልን እየደሰኮርን፣ በየቦታው በቅርብ ርቀት የጉድጓድ ውኃ ማግኘት የሚቻልበት ተፈጥሯዊ ፀጋ እያለን፣ ከጧት እስከ ማታ በሬ ጠምዶ ውሎ የማይደክመው ታታሪ አምራች ገበሬ እያለን፣ በብልኃት፣ በአስተዳደርና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ችግር ምክንያት ስንዴ የምናስመጣ፣ ፓስታና መኮሮኒ ከውጭ አገር የምናስገባ፣ ሽንኩርት ሳይቀር ከሱዳን ማስገባት የጀመርን አገር ሆነናል። በየዓመቱ በርካታ ቶን የቅባት እህል በጥሬው ኤክስፖርት እያደረግን የፓልም ዘይት በውጭ ምንዛሪ የምናስመጣ ነን። ሀብቱ በእጃችን እያለ በትኩረት ማነስ መፍትሔ ያላገኘ ጉዳይ ነው ያለን። በቅርብ ጊዜ የግብርና ሜናካይዜሽን ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡና የልማት ባንክም ለእነዚህ ብድር እንዲሰጥ እየመጡ ያሉ መመርያዎች ወደፊት ተስፋ ሰጪ ከመሆናቸውም ባሻገር፣ የገነባናቸው የግብርና ማቀነባበሪያና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ያለ በቂና አስተማማኝ የግብርና ምርት አቅርቦት ከፈረሱ ጋሪውን ማስቀደም ስለሚሆን፣ የግብርና ፖሊሲያችንን ባለን ተፈጥሮአዊ ፀጋ ልክ መቃኘት ይጠይቃል። የገነባናቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮች ጨርቁን እዚህ አምርተው መጠቀም እንዲችሉ የጥጥ ግብርና በአግባቡ በፖሊሲ ተደግፎ መመረት ይገባዋል። አገር ውስጥ ላሉ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች እንኳን በቂ የሆነ የጥጥ ምርት አለማምረት ብቻ ሳይሆን፣ በተለያዩ ምክንያቶች የተመረተውን ጥጥ ፋብሪካዎቹ ባለመግዛታቸው የእኛን ጥጥ

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

**የሌሎች ሽቀጥ ማራገፊያ ....... ከገጽ 7 የዞረ**

ኤክስፖርት ስናደርግና ከውጭ አገር ደግሞ ጥጥ ስናስመጣ በዚህ መሀል ማየት ያለብንን አቅጣጫዎች መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይ ያለ ግብርና ልማት ኢንዱስትሪን ዕውን ማድረግ የሚታሰብ ባለመሆኑ፣ ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ የተሰጠውን ትኩረት ያህል ሊሰጠው ይገባል፡፡

***ሪፖርተር፡-*** *ያለ ግብርና የኢንዱስትሪ ልማትን ማሰብ አይቻልም የሚለው ነጥብ ትክክል ነው? እንዴት?*

**ኢንጂነር መልአኩ፡-** በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ የእንስሳት ሀብቱንም ስንመለከት በግብዓት ሰንሰለት ከጥንት ችግር በሕገወጥ ንግድ ምክንያትና በመሳሰሉ በአገራችን ትልቅ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ሊሆነን በሚቻለው መስክ፣ ጎረቤት አገሮች በኮንትሮባንድ እየወሰዱት በኢትዮጵያ ወርቅ እነሱ እየደመቁ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእንስሳት ሀብት በቁጥር አንደኛ ነን እያሉ ከመናገር አልፈን በውጤታማነትና በምርታማነት ላይ በመሥራት በአሁኑ ጊዜ ከ90 በመቶ ያላነሰ የአገሪቱን የወተት ፍላጎት ከውጭ አገር በሚመጣ የወተት ዱቄት እያሟላን መቀጠል ያለብን አይመስለኝም፡፡ በርካታ የቄራ ኤክስፖርት ድርጅቶች ቢኖሩም፣ በአቅርቦት እጥረት ብዙ ጊዜ የሚያማርሩት አንደኛ በቁሙ መላክ ነጋዴው ስለሚፈልግ፣ ሁለተኛ ሕገወጥ ንግዱ፣ ሦስተኛ በቂ የሆነ በመላው አገሪቱ የእንስሳት ማራቢያና ማሳደጊያ ማዕከል አለመገንባታችን የግብይት ሰንሰለቱና ኢንቨስትመንቱ እንዲዳከም አድርጎታል፡፡

በመሆኑም ከእንስሳት ሀብት ልማት ጋር የተያያዙ አሳሪ ሕጎችና መመርያዎች ቢቃኙ ዘርፉ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት፣ በሚሊዮን የሚቆጠር የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ገቢ ምርቶቻችን በመቀነስ (Import Substitution)፣ ብሎም ኦርጋኒክ ምግቦችን የሚመገብ ጤናማ ዜጋ በመፍጠር የአገራችን ኢኮኖሚ ማሳደግ ይቻላል፡፡ ከደን ልማት ጋር በተያያዘ ደን እየጨፈጨፍን ጣውላ፣ ስቲኪኒና ችፑድ እንደማስመጣት የሚያሳፍር ነገር የለም፡፡ ስለዚህ በገበያ ደረጃ ለደን ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ግብዓት ሊሆን የሚችል ቢቂና አስተማማኝ የደን ሀብት ልማት ላይ በማተኮር የአገራችንን የቤትና የቢሮ ዕቃዎች፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ችግር በመፍታት በየዓመቱ ከውጭ አገር የሚመጣውን መቀነስ ብቻ ሳይሆን፣ ኤክስፖርት በማድረግ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ መሆን ስለሚችል ያሉብንን ክፍተቶች በመገምገም የፖሊሲ ማዕቀፉን አሠሪ አድርጎ መቅረፅ ይጠይቃል፡፡ እነዚህ ተፈጥሯዊ ሀብቶች አገራችን ኢትዮጵያ የታደለችበትን የበለጠ በማልማትና በፖሊሲ መደገፍ ሲቻል አብዛኛው አምራች ኢንዱስትሪ ማለት ይቻላል ግብዓት የሚወስደው ከግብርና ምርቶች፣ ከደንና ከእንስሳት ሀብት መሆኑን ስናስብ፣ አገራችንን በእነዚህ ዘርፎች የልህቀት ማዕከል ማድረግ ስንችል ተመራጭ የንግድና ኢንቨስትመንት ማዕከል ያደርጋታል፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ሌላው ቢቀር በምግብ ራሳችንን በመቻል ምግብ ርካሽ መሆን የሚቻልበትን መንገድ መፍጠር ይቻላል፡፡ ዞሮ ዞሮ ድሆች ሳንሆን ሀብታችንን በዕውቀትና በዘመናዊነት ባለመምራት በጊዜው ያጋጠሙንን ተግዳሮቶች በዕውቀትና በክህሎት በመምራት ከእግዚአብሔር ጋር መጪውን ዘመን መሻገር ይቻላል፡፡ መንግሥትም ቀደም ብዬ ለጠቀስኳቸው ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በሙሉ ትኩረት በመስጠት፣ የፖለሲ ማሻሻያ ሐሳቦች ላይ ጠንክሮ እየሠራ ይመስለኛል፡፡

---

**"የንግድና ኢንቨስትመንት ኢንፎርሜሽን ሊያገኙ የሚችሉበትን የመረጃ ማዕከል በምክር ቤቱ 7ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 114 በመሄድ እንዲጎበኙ በአክብሮት ተጋብዘዋል"**

**አገልግሎት የሚሰጥበት ሰዓት፡ ከሰኞ-አርብ ከ3-11 ሰዓት**

**ዋና አዘጋጅ፡- ደበበ አበበ**
**አዘጋጆች፡- ዮሴፍ ተሸመ**
**ጥበቡ ታዬ**
**ካሜራ፡- ያሬድ አባቡ**
**ፕሮቶኮል፡- ሲሳይ አስታጥቄ**

**አድራሻ፡-**
**ስልክ-፡- +251-115-54-09-93**
**ፋክስ፡-+251-011-5517699**
**ኢሜል፡- ethchamb@ethionet.et**
**ድረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com**